# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 158 ግንቦት 18 2003 ገጽ 1

**የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) ሰሞኑን ይፋ ባደረገው የጥናት ውጤት መሠረት ከ1990 እ.ኤ.አ. ወዲህ በነበሩት 18 ዓመታት ውስጥ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከኢትዮጵያ ወጥቷል። ይህ ማለት ዩ.ኤን.ዲ.ፒ በጥናት ደረስኩበት እንዳለው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ተቆጣጥረው የድሆችን ደም እየመጠጡ ያሉ ሰዎች 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከአገር አሸሽተዋል ማለት ነው። ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ**

## ወያኔ የሚያከብረውን 20ኛ የድል አመት አስመልክቶ ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ

## ሃያ የክህደት፣ የውርደት፣ የዘረኛነትና የዘራፊነት አመታት

በደርግና በመንግስቱ ሃይለማሪያም ቦታ ወያኔና መለስ ዜናዊ ከተተኩ 20 አመት ሆነው። ሰሞኑን መለስ ዜናዊ ሃያኛውን የንግስና በአል ለማክበር ከፍተኛ በጀት መድቦ እየተራወጠ ነው። የፈረደበት ህዝብም በአሉን እንዲያጅብ በየቀበሌውና በየመስመሪያ ቤቱ ቀጭን ትእዛዝ ደርሶታል። ያው መንግስቱና ኢሰፓ ሲያደርጉ እንደነበረው ማለት ነው። ዛሬም እንደ ትናንቱ ህዝብ የሃገሩንና የራሱን አራጆቹ ድግስ እንዲያሞቅና ለዲስኩራቸው እንዲያጨበጨብ እየተደረገ ያለው ሠራተኛው በደሞዙ፤ ሌላው ከቀበሌ በሚያገኘው ስኳር፣ ዘይትና ሌሎችም አግልግሎት በኩል በሚመጣበት ማስፈራሪያ ነው። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሃገሪቱ ህዝብ በማንኛውም የህይወት ዘርፍ ያለመለስ ዜናዊ ካድሬዎቹ ሳንባ መተንፈስ እንዳይችል የሚያደረገው ሽምቀቆ እየጠበቀ ሄዷል። ብቸኛው ቀጣሪ፤ ስኳርና ዘይት አከፋፋይ፤ የእድገትና የከፍተኛ ትምርት እድል ደልዳይ፤ ፍትህንና የባንክ ብድርን ፈቃጅ ወያኔ ብቻ በሆነበት ሃገር ህዝብ ምርጫው ሰልፍ መውጣት፤ ለወያኔ ገንዘብ ማዋጣት፤ ወያኔ የሚያዘውን ሌላም ትእዛዘ መፈጸም ሆኗል። ይህ ግን እውነታውን አይደብቀውም። ከወያኔ የሻምፓኝ፣ የሽቶ፣ የከበሮ፣ የእልልታና የፉከራ ድግስ ጀርባ ያለው የስርአቱ አስከፊ ገጽታና ክርፋት መሸፋፈኛዎቹን ሰብሮ በአይን መታየቱ በአፍንጫ መሽተቱ አልቀረም።

ያለፉት ሃያ አመታት ለኢትዮጵያ እንደምን ያሉ አመታት ነበሩ?

1. ሃያ የወያኔ አመታት ለመጀመሪያ ግዜ በሃገራችን ታሪክ ከአንድ ዘር ብቻ የተሰባሰቡ ጥቂት ግለሰቦች የሃገሪቱን ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ስልጣን፤ የሃገሪቱን ሃብት፣ መሬቱንና ማዕድኑ፤ የሃገር ውስጥና የወጭ ሃገር ንግዱን፤ የኮንስትራክሽን፣ የባንክ፣ የኢንሹራንስ፣ የትራንስፖርት፣ የማምረቻና ማከፋፈያ ስራውን የተቆጣጠሩበት፤ እፍረትና ይሉኝት የለሽ ነውረኛና አደገኛ ስራ የተሰራባቸው አመታት ናቸው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## የኑሮ ዉድነት ከመቼውም ጊዜ በላይ የከፋ ደረጃ ላይ ደረሰ፣ በአዲስ አበባ ከተማ ዘይትና ስኳር የቅንጦት እቃዎች ሆነዋል

ኢትዮጵያዊያን በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የኑሮ ውድነት አዘቅት ውስጥ መውደቃቸውን የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ገለጸ። መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎች የሆኑትን ዘይትና ስኳርን ፈልጎ ማግኘት እንደማይቻልና ቢገኙም ዋጋቸው በጭራሽ የማይቀመስ እየሆነ በመምጣቱ ህብረተሰቡ ሰርቶ ከሚየገኘዉ ገቢ ዉስጥ አብዛኛዉን ለዋጋ ንረቱ ማካካሻ ለማድረግ መገደዱን ከወደ አዲስ አበባ የሚመጡ ዜናዎች ያስረዳሉ።

በተለያዩ የአዲስ አበባ ክፍለ ከተሞች በመዘዋወር ሸማቹን ህብረተሰብና የሸቀጣ ሸቀጥ ቸርቻሪዎችን ያናገረው ዘጋቢያችን እንደገለጸው፡ በአገሪቱ ውስጥ እስከዛሬ ድረስ ታይቶ ለማይታወቀው ለዚህ አይነቱ የፍጆታ እቃዎች ከገበያ መጥፋት ዋነኛዉ ምክንያት የወያኔ አገዛዝ ከገበያ ስርአት ዉጭ ህዝብ ይወደኝ ይሆናል በሚል ቅዠት ብቻ ነጋዴዎች እቃቸዉን ከገዙበት ዋጋ በታች እንዲሸጡ በማስገደዱ እንደሆነ ታውቋል። አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች እንደገለጹት ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ሙሉ በሙሉ ከተዘፈቀበት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና፣ የማህበራዊ ቀውሶች ውስጥ ነጋዴውንና ሸማቹን በማጋጨት መውጫ የሚያገኝ መስሎት በግብታዊነት በወሰደው እርምጃ አብዛኛውን የህብረተሰብ ክፍል ለባሰ ችግር ዳርጎታል።

ይህ ዛሬ ኢትዮጵያ ዉስጥ የተፈጠረው የፍጆታ ሸቀጦች ከገቢያ ላይ መጥፋት ባጋጣሚ ብቅ ያለ ሳይሆን ወያኔ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት አስቦ ሆን ብሎ የፈጠረው ችግር እንደሆነ አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ይናገራሉ። ወያኔ የእያንዳንዱን ኢትዮጵያዊ ህይወት ለመቆጣጠር እንዲያስችለው ከገቢያ ላይ እንዲጠፉ ያደረጋቸውን ሸቀጦች "የሸማቾች ማህበራት" በሚል ስም እራሱ ባቋቋማቸው ድርጅቶች አማካይነት እያከፋፈለ እንደሚገኝና ይህም አዲስ ዘዴ መለስ ዜናዊ በይፋ እንደተናገረዉ መንግስት የግሉን ክፍለ ኤኮኖሚ ለመተካት የጀመረዉ ዕቅድ አካል እንደሆነ ሪፖርተራችን ከላከልን ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የህዳሴ ግድብ የተባለው የወያኔ መፎከሪያ ለመስኖ አገልግሎት እንደማይውል ሃይለማሪያም ደሳለኝ ገለጸ

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በምክትል ጠቅላይ ምንስትርነትና የውጪ ጉዳይ ምንስትርነት ለይስሙላ የሾመው ሃይለማሪያም ደሳለኝ ባለፈው ሳምንት ለጋዜጠኞች በሰጠው መግለጫ የህዳሴ ግድብ በፍጹም ለመስኖ አገልግሎት አይውልም፣ በዚህም ምክንያት ግብጽ ምንም አይነት ጥርጣሬ ሊገባት አይገባም ማለቱ ብዙዎችን የሥርዓቱን ደጋፊዎች ማሳዘኑን ለማወቅ ተችሎአል።

በአንድ ወር ሁለት ስም የተሰጠው የአባይ ግድብ ግንባታ ከውጥኑ ጀምሮ ምንም አይነት ጥናት እና ዝግጅት ያልተደረገበት ሌላው ቀርቶ በራሱ የወያኔ የአምስት አመት የልማትና የእድገት ትራንስፎርመሽን እቅድ ውስጥ ያልተካተተ በመሆኑ ቀድሞውኑ በርካቶች ትክክለኝነቱን ሲጠራጠሩት የቆዩ ቢሆንም በአገዛዙ ቁንጮዋች በየእለቱ የሚሰጡ እርስ በርሳቸው የተምታቱ ገለጻዎች በየዋህነት ስለግድቡ አምነው የነበሩትን እያስከፉ መምጣቱን ለወያኔ ቅርበት ያላቸው ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የሲዳማ ነጻነት ግንባር በአዋሳ በ1994 የተደረገውን ጭፍጨፋ በማሳወስ መግለጫ አወጣ

የስዳማ ነጻነት ግንባር |ሲነግ| ከትናንት በስቲያ ግንቦት 16 ቀን 2003 አም የዛሬ 9 አመት በአዋሳና አካባቢው ነዋሪዎች ላይ በወያኔ ባለስልጣናት ትዕዛዝ የተፈጸመውን ጭፍጨፋ በማስመልከት መግለጫ አውጣቶአል።

በሰላማዊ ሰልፍ ተቃውሞአቸውን ለመግለጽ ተነስተው በነበሩት ሰላማዊ ዜጎች ላይ በጠራራ ጸሃይ ለተፈጸመው ጭፍጨፋ ዋና ተጠያቂዎች በረከት ስምዖን ፤ሙሉጌታ አለምሰገድ፤ ታደስ ካሴ፤ አባዱላ ገመዳ፤ ግርማ ብሩ፤ ሃይለማሪያም ደሳለኝ፤ መለሰ ሚራሞ እና ሺፈራው ሽጉጤ ናቸው ያለው መግለጫ ሁሉም ተጠቃሾች የስዳማን ህዝብ በማስፈጀት እጃቸው በደም የተጨማለቀ ወንጀለኞች ናቸው ብሎአል።

ለመብቱ ተቆርቋሪ የሆነውን የሲዳማን ህዝብ ትግል ለመደፍጠት በተወሰደው የሃይል እርምጃ ብዙዎች በረቀቀ ዜዴ ተገለዋል ፤ ታስረዋል ፤ አገራቸውንም ጥለው ለመሰደድ ተገደዋል ያለው የስዳማ ነጻነት ግንባር ፤ ይህ ሁሉ ግፍ የተፈጸመው ህዝባችን በወያኔ አገዛዝ ላይ እንዳይተባበር ለማድረግ ነው ሲል ከሶአል። በመጨረሻም ታሪክ በአዋሳ ሎቄ መንደር የተፈጸመውን ጭፍጨፋ ይቅር እንደማይለው ገልጾ እነኚያ በግፍ የተጨፈጨፉት ሰማዕታት ዘወትር ሲታወሱ እንደሚኖሩና እነርሱ የተሰውለትን የመብት ጥያቄ አንግቦ በትግሉ እንደሚገፋበትና የነጻነትን ቀን ለማቃረብ እንደሚታገል አረጋግጦአል።

## ዲሞክራሲ በአገራችን እንዲሰፍን የሚታገሉ 9 ተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች እና የስቪክ ድርጅቶች የመለስ ዜናዊ ዘረኛ እና አምባገነናዊ አገዛዝ እንዲያበቃ ባለ 8 ነጥብ የአቋም መግለጫ በየድርጅቶቻቸው ስም አወጡ

በቅርቡ ቱኒዝያና ግብፅ ዉስጥ መለስ ዜናዊን የመሳሰሉ ፀረ-ህዝብ የሆኑ አምባገነን መሪዎችን የጠራረገዉ ህዝባዊ አብዮት ኢትዮጵያ ዉስጥም በቅርብ ግዜ ዉስጥ መፈንዳቱ የማይቀር መሆኑ የታያቸዉ 8 ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ስቪክ ድርጅቶች፤ ይህንን አይቀሬ ህዝባዊ እንቅስቃሴ አስተባብሮ ለመምራት በሚያስችላቸው የጋራ አጀንዳ ላይ በተናጠል ሲመክሩ ከቆዩ የጋራ የመታገያ መልዕክት ያለው ባለ8 ነጥብ የአቋም መግለጫ በየድርጅቶቻቸው ስም ማውጣታቸው ተገለጸ።

**"በህዝባዊ አንድነትና በጋራ አላማ የሚመራ የእምቢተኛነት ቁጣ ካለመበት ይደርሳል"** የሚል አርዕስት የወጣዉ ይህ የተቃዋሚዎች መግለጫ፡ የታሰሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ በአስቸኳይ እንዲፈቱ ከመጠየቅ አንስቶ መለስ ዜናዊና ቤተሰቦቹ ከደሃዉ ህብረተሰብ ዘርፈዉ ያካበቱት ሃብት በሙሉ እንዲወረስ፤ (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ከኢትዮጵያ በህገወጥ መንገድ መውጣቱ የተጋለጠው ከአንድ መቶ ሃምሳ ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ አነጋጋሪ ሆኑአል፣ ኢትዮጵያዊያን በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ላይ መነሻ ጊዚያቸው አሁን ነው ተባለ

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት መርሃ ግብር (UNDP) በቅርቡ ባወጣዉ ጥናታዊ ሪፖርት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ስልጣን ላይ በቆየባቸዉ ባለፉት ሃያ አመታት ዉስጥ ብቻ 8.4 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወይም ከአንድ መቶ ሰላሳ ስምንት ቢሊዮን ብር በላይ የሆነ ገንዘብ ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ከአገር ወጥቶ በዉጭ አገር ባንኮች መከማቸቱን ይፋ አደረገ። ይህ ወዳጅንም ሆነ ጠላትን ያስደነገጠ ዜና በርካታ ኢትዮጵያዊያን ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት እንዲሰጡት ከማድረጉም በላይ የህንን ዘረኛና ዘራፊ አገዛዝ ለመገረሰስ የሚደረገዉን ትግል በበለጠ ያጠናክረዋል ሲሉ አንድ ስማቸው እንዳይገለጽ የፈለጉ ባለሙያ ለግንቦት ሰባት ዘጋቢ ገለጹ።

በአሜሪካኗ መናገሻ ዋሽንግተን ዲሲ ዉስጥ የሚገኝ የአንድ አለም አቀፍ ተቋም ሠራተኛ የሆኑት እኚህ ባለሙያ ለዘጋቢያችን እንደገለጹት- የዋጋ ግሽበት ከቁጥጥር ዉጭ በሆነበትና አብዛኛው ህዝብ ጠግቦ በማያድርበት አገር ዉስጥ መሪ ተብዬዎች ይህንን የመሰለ መጠነ ሰፊ የሆነ ገንዘብ በህገ ወጥ መንገድ ከአገር የማሸሻቸው ጉድ የወያኔን ልማታዊነት ደጋግሞ በተናገረዉ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት መርሃ ግብር አፍ መነገሩ መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ በአገራችን ላይ እየፈጸሙ ያሉት ወንጀል ምን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ያሳያል ብለዋል።

እኚሁ ሰዉ አያይዘው እንደተናገሩት፤ በአንድ በኩል ወያኔ የህዝብን የትኩረት አቅጣጫ ለማስቀየር ሲል ብቻ በአንድ ጀምበር ላቀደዉ የአባይ ግድብ ማሰሪያ ረሀብ ያደቀቀዉን ህዝብ ቦንድ ካልገዛችሁ ብሎ እያስገደደ በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣናትና ወዳጆቻቸዉ የህዳሴዉን ግድብና ሌሎች ተጨማሪ አምስት ግድቦችን መስራት የሚችል እጅግ በጣም ከፍተኛ ቁጥር ያለዉ የህዝብ ገንዘብ ዘርፈዉ በኃብታም አገሮች ባንኮች ዉስጥ ማከማቸታዉ እጅግ የሚያሳፍርና አይን ያወጣ የሌብነት ተግባር ነዉ ብለዋል።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዝርፊያ በቃ!!!!

የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) ሰሞኑን ይፋ ባደረገው የጥናት ውጤት መሠረት ከ1990 እአአ ወዲህ በነበሩት 18 ዓመታት ውስጥ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከኢትዮጵያ ወጥቷል። ይህ ማለት ዩ.ኤን.ዲ.ፒ በጥናት ደረስኩበት እንዳለው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ተቆጣጥረው የድሆችን ደም እየመጠጡ ያሉ ሰዎች 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከአገር አሸሽተዋል ማለት ነው።

የኢትዮጵያ ገዢዎች የኢትዮጵያን ሃብት እየዘረፉ በውጭ አገራት እንደሚያከማቹ ተደጋግሞ የተነገረ ቢሆንም እነሱ ግን ሲያስተባብሉ ቆይተዋል። አሁን ግን "የፈጣን እድገት" መዝሙራቸውን የሚያዳምቅላቸው ዩ.ኤን.ዲ.ፒ ሳይቀር ይህን ያህል ገንዘብ ከድሃው ጉሮሮ መዝረፋቸው አጋልጧል።

ለመሆኑ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ምን ያህል ነው?

- 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር በዛሬ ምንዛሪ ወደ 150 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ይሆናል።
- 3 ሚሊዮን ብር የተሟላ የጤና ጣቢያ ይገነባል። በተዘረፈው 150 ቢሊዮን ብር 50, 000 የጤና ጣቢያዎችን መገንባት ይቻል ነበር።
- በ 1 ሚሊዮን ብር አንድ የተሟላ የአንደኛ ደረጃ ት/ቤት ይሰራል። በተዘረፈው 150 ቢሊዮን ብር 150, 000 አንደኛ ደረጃ ትምርህርት ቤቶች መሠራት ይችሉ ነበር።
- የእድገትና ትራንስፎርሜሽ እቅድ በተሰኘው ሰነድ አገሪቱን ከጫፍ እስከጫፍ በባቡር ለማገናኘት ያስፈልጋው ተብሎ የተያዘው በጀት 170 ቢሊዮን ብር ነው። የተዘረፈው ገንዘብ የባቡር ሃዲዱን ማሠሪያ ወጪን 88 በመቶ ይሸፍን ነበር ማለት ነው።
- ህዝብን እያራቆተ ያለው የህዳሴ ግድብ ያስወጣል የተባለው 80 ቢሊዮን ብር ነው። የተዘረፈው ገንዘብ ይህንን የተረት ግድብ ወጪን ሸፍኖ በአዋሽና በተከዜ ወንዞች ላይ ለመስኖ የሚያገለግሉን አራት ተጨማሪ መለስተኛ ግድቦችን ይሰራ ነበር።

ይህን ያህል ሃብት ነው መለስ እና ግብረ አበሮች በ18 ዓመታት ከኢትዮጵያ እንዳሸሹ ዩ.ኤን.ዲ.ፒ የነገረን።

ለመሆኑ ዩ.ኤን.ዲ.ፒ ራሱ ቁጥሩን በትክክል ደርሶበታል? የመለስ ዜናዊ ቡድን፦

- በረሃ እያለ ጀምሮ አሸዋ የሞሉ ከረጢቶችን እህል ነው እያለ ለእርዳታ ድርጅቶች በመሸጥ የስርቆት ልምድ ያካበተ ድርጅት መሆኑ፤
- እጅግ ለም የሆነ መሬት በሄክታር ከአስር ዶላር ባነሰ የሊዝ ዋጋ ለአረቦችና ህንዶች ሰጠሁ ብሎ በአደባባይ ቢናገርም "ውስጥ ውስጡን ምን ያህል ይሆን ያስከፍለው ?" የሚል ጥያቄ ማስነሳቱ የማይቀር መሆኑ፤
- በቅርቡ ለውጭ ንግድ ቀርቦ የነበረ አስር ሺህ ቶን ቡና የደረሰበት ሳይገለጽ ተሸፋፍኖ መቅረቱ እና በዚህ ደረጃ ዘረፋ ለማካሄድ ፍላጎትም አቅምም ያለው መሆኑን ሲታሰብ፤
- አገሪቱ የገጠማትን የኑሮ ፈተና በመወጣት እና የዋጋ ግሽበትን በማረጋጋት ረገድ ትልቅ ሃገራዊ አስረዋጽዖ ሊኖራቸው ይችሉ የነበሩትን የወርቅ ማዕድኖችን እዚህ ግባ በማይባል ዋጋ የአላሙዲ ንብረት ለሆነው ሚድሮክ መሸጡ እና በተለያዩ ደረጃዎች በፈጠራቸው ሽርክናዎች የጥቅም ተካፋይ እንደሆነ ሲታሰብ፣
- አሜሪካ የሰጠችውን የኦጎዋ ኢኒሼቲብ ተጠቃሚዎች አልሜዳና መሰል የወያኔ ካምፓኒዎች መሆናቸው እና የመሳሰሉትን ተጨማሪ ነገሮችን ሂሳብ ውስጥ ስናስገባ የ ዩ.ኤን.ዲ.ፒ ጥናት የዘረፋውን አንድ አስረኛ እንኳን መሸፈኑን እንጠራጠራለን።

ይሁን እንጂ የዘረፋውን ሙሉ ገጽታ ባያሳይም የ ዩ.ኤን.ዲ.ፒ ጥናት በብዙ ጎኑ ዓይን ከፋች ነው። ዘረፋው ከምርጫ 97 ወዲህ እየጨመረ መምጣቱ ራሱ ብዙ የሚናገረው ነገር አለ። ዛሬ በአውሮፓና አሜሪካ ከተሞች ቤቶችን ያልገዙ፤ የባንክ ሂሳብ ያልከፈቱ የወያኔ ሹማምንት የሉም።

ጥናቱ ይፋ ያደረገው ሌላም አቢይ እውነታ አለ። ይህም ዘረፋ አብዛኛው የተካሄደው በንግዱ ማኅበረሰብ አካላት በተለይም በወጪና ገቢ ንግድ ወቅት በሚቀርቡ የሃሰት ደረሰኞች ነው መባሉ ነው። ይህ ጠቃሚ ነጥብ ነው። ለእንዲህ ዓይነቱ ዘረፋ መንገድ የተመቻቸለት የትኛው ነጋዴ ነው?

እንደሚታወቀው በመዝገብ እና በስም የወያኔ እና የአላማሙዲን ኩባንያዎችም "ነጋዴዎች" ናቸው። ይህንን የንግዱ ማህበረሰብ እንዴት ይመለከተዋል? ሌላውስ ኢትዮጵያዊ እንዴት ይታገሰዋል?

ከዚህ በፊት የምናውቀው ዘረፋውን ሙሉ በሙሉ ያልሸፈነ ቢሆንም እንኳን የዩ.ኤን.ዲ.ፒ ጥናት ውጤት ይፋ መደረጉ በጣም ጠቃሚ ነገር ነው። የወያኔን ዓይን ያወጣ ዘረፋን ለማጋለጥ አንድ ተጨማሪ ማስረጃና ግብዓት ይሆነናል።

ቀሪው ሥራ ያለው እኛው ዘንድ ነው። ይህንን መረጃ እንዴት ነው የምጠቀምበት? ንብረታችን ሲበዘበዝ እያየን እስከ መቼ በዝምታ እናልፋለን?

ዝርፊያ በቃን!!!! ዘራፊዎችን ለፍርድ ለማቅረብ የተቀነባበረ ሥራ እንሥራ! ንብረታችን ለማስመለስ የሚያስችሉንን ተጨባጭ እርምጃዎች እንውሰድ! በዝርፊያ የቆመውን የመለስ ዜና አገዛዝን እናስወግድ!

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጊዴስ!!!**

### የኑሮ ዉድነት ከመቼውም ጊዜ በላይ የከፋ ደረጃ ላይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እነዚህ ወያኔ ያቋቋማቸዉ የሸማቾች ማህበራት በአስቤዛ መልክ የሚያከፋፍሉትን ስኳርና ዘይት ለማግኘት ያለዉ ሰልፍ እጅግ በጣም ረጅም ከመሆኑም በላይ አከፋፋዮቹ አገዛዙን ይቃወማሉ የሚባሉ ሰዎችን ለይተው ጫና እንደሚያደርጉባቸው ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል። የፍጆታ ሸቀጦቹ ከገቢያ መጥፋት በአገሪቱ ውስጥ እያነሳሳ ያለው ህዝባዊ ቁጣና ብሶት ያስደነገጠው ዘረኛው መለስ ዜናዊ ለዕጥረቱ መፈጠር ነጋዴውን ህብረተሰብ ተጠያቂ ለማስመስለ ባለፈው ሰኞ ግንቦት 15ቀን ነጋዴዎችን ሰብስቦ ሲፈነጭባቸው እንደዋለ በቴለቪዥን ከተላለፈው ንግግሩ ለመረዳት ተችሎአል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የዘይት ሃይቅ በመፍጠር ሃገሪቱን በዘይት የማጥለቅለቅ እቅድ እንዳለው የገለጸው የህወሃት ቁንጮ በንግዱ መስክ የተሰማሩትን የአገሪቱ ዜጎች እንደማያምን ያለምንም ሃፍረት አረጋግጦአል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለይም በሰሜን አፍሪቃ የተነሳው ህዝባዊ አመጽ በበርካታ ሃገራት ከተቀጣጠለ ወዲህ፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ተመሳሳይ ህዝባዊ አመጽ ይነሳብኛል በሚል ፍራቻ እንቅልፍ ማጣቱና ከተፈጠረበትም ጭንቀት መውጫ መንገድ ፍለጋ በርካታ አስገራሚና አደናጋሪ ርምጃዎችን በግብታዊነት ሲወስድ መቆየቱ በስፋት መዘገቡ ይታወስል::

### ዲሞክራሲ በአገራችን እንዲሰፍን የሚታገሉ 9 ተቃዋሚ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ህገ ወጥ በሆነና በተጭበረበረ ምርጫ የተቋቋሙት የህዝብ መወሰኛና የፌደራል ምክር ቤቶች በአስቸኳይ እንዲፈርሱ፤ መለስ ዜናዊ ከጠቅላይ ሚንስትርነት ስልጣኑ ተነስቶ በምትኩ አላማና ግቡ ፍትህ፤ነፃነት፤ ዲሞክራሲና እኩልነት የሆነና የነጻነት ንቅናቄዎች፤ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበረሰብ ተወካዮች የሚሳተፉበት አገሪቱን ነፃና ዲሞክራሲያዊ ለሆነ ምርጫ የሚያዘጋጅ የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም የሚጠይቅ ነዉ።

ይህንን ባለ 8 ነጥብ የጋራ መግለጫ የጋራ መታገያ አጀንዳቸዉ እንደሆነ አስምረውበት በየግላቸው መግለጫውን ያወጡት ድርጅቶች ፡ ጥምረት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትህ በኢትዮጵያ (ጥምረት) ፤ የትግራይ ህዝብ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ትህድን)፤ የኦሮሞ ነጻነት ግንባር (ኦነግ)፤ የአማራ ዲሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ(አዲሃን)፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር፤ ትንሳኤ ኢትዮጵያ የአርበኞች ህብረት፤ አለማቀፍ የሲቪክ ንቅናቄ በኢትዮጵያ እና ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ናቸው። እነዚህ ከላይ ስማቸው የተዘረዘረው ስምንት ድርጅቶች ያወጡት የመታገያ አቋም ቀደም ሲል በኦሮሞ ወጣቶች ንቅናቄ ይፋ ተደርጎ የነበረና ሁሉም ድርጅቶች በጋራ መታገያነት የተስማሙበት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

### የህዳሴ ግድብ የተባለው የወያኔ መፎከሪያ ለመስኖ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ሃይለማሪያም ደሳለኝ ይሰራል በተባለው የአባይ ግድብ ላይ ምንም መስኖ የመጠቀም እቅድ እንደሌለ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን የሰጡን ስማቸው እንደይገለጽ የጠየቁ አንድ የአካባቢ ሳይንስ ምሁር፣ እንደገለጹት የአባይ ታላቅ ግድብ ተብሎ ተሰይሞና፣ የግድቡ የውሃ ከምቹትም የጣና ሃይቅን እጥፍ ይሆናል እየተባለ የተወራለት ግድብ፣ በምንም አይነት መልኩ ለመስኖ አገልግሎት አይውልም መባሉ ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በየአመቱ በረሃብ አለንጋ ለሚቀጠፈው ኢትዮጵያዊያ ህይወትና አገራችን ለምትታወቅበት ረሃብተኝነት ምንም ቅንጣት እንደሌለው የሚያሳይ ፣ እውነት አባይን መገደብ ብንችል ስለግድብ ሙያዊ እውቀት ላላቸው ምሁራን ያለውን ከፍተኛ የሆነ ንቀት የሚያሳይ ነው ብለዋል።። በመቀጠልም በመሰረቱ ኢትዮጵያ ከድህነትና ረህብ አረንቋአ እንድትወጣ ከተፈለገ ሃገሪቱ ያላትን የውሃ ሃብት ለኤሌክትሪክ ሃይል እየተጠቀምች ጎን ለጎን ለመስኖ ልማት መጠቀም የማትችልበት ምክንያት ፈጽሞ ሊኖር አይችልም ብለዋል። ዳሩ ግን ወያኔ የአገር ጥቅም ያስጠብቃል ተብሎ ስለማይታሰብ ፤ ያለፈው የ20 አመት ታሪኩም የሚያሳየው ለም የአገሪቱን መሬት ለባ ዕድ አገር ባለሃብቶች አሳልፎ ሲሸጥ፤ በድንበር አካባቢ ያለውን ወሰን መሬት እንደገና ዳቦ ለጠየቀው ሁሉ የሚሰጥ ሃይል ስለሆነ ከአሁን ቦኋላ ተሃዲሶ አድርጎ ይለወጣል የሚል ተስፋ ማናችንም የለንም ብለዋል።

ይህ በ እንዲህ እንዳለ በደቡብና በደቡብ ምሥራቅ የአገራችን አካባቢዎች በተከሰተው ድርቅ ሣቢያ የምግብ እርዳታ ፈላጊው 3 ነጥብ 2 ሚሊየን እንደደረሰ ፤ ቀደም ሲል የዓለም የምግብ ፕሮግራም እርዳታ እያደረገላቸው ያለውን ተረጂዎች ስጨምር በዚህ ዓመት አጠቃላዩ ተረጂ ቁጥር 4 ነጥብ 3 ሚሊየን መሆኑን የዓለም የምግብ ፕሮግራም ማስታወቁን ቪ ኦ ኤ ከትናንት በስቲያ ባወጣው ዘገባ ላይ ገልጾአል፡፡ እንደ ቪ ኦ ኤ ዘገባ የዘንድሮው ድርቅ መንስዔ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆየው የክረምት ዝናብ አንድም አነስተኛ መሆኑ፣ አልያም አሁንም በድርቅ በተጠቁት አካባቢዎች ከመደበኛው በታች የዓለም የምግብ ፕሮግራም ቃል አቀባይ መግለጻቸውና በዘንድሮው ድርቅ የተጠቁት አካባቢዎች ፈጥነው ያገግማሉ ብለው እንደማይጠብቁና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሰብዓዊ እርዳታና የምግብ አቅርቦት የሚፈልገው ሰው ቁጥር ሊጨምር እንደሚችል ታውቁአል።

ህዝብ በየአመቱ ለእንዲህ አይነት አስከፊ ረሃብ አደጋ በሚጋለጥበት አገር ስልጣን ላይ ያለው መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ ከ8 ነጥብ 5 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ዘርፈው በህገ ወጥ መንገድ ከአገር እንዳሸሹ ዩ ኤን ዲፒ የተባለው የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት አስታውቆአል።

### የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ተራ ግድያ በመፈፀም ላይ እንዳለ የኦጋዴን ነፃነት ግንባር ገለ

በመለስ ዜናዊ አገዛዝ የታዘዙ የኢትዮጵያ ወታደሮችና ፖሊሶች በሱማሌ ክልል የነዳጅ ፍለጋ በሚካሄድባቸዉ አካባቢዎች የሚገኙ መንደሮችን በመዉረር ሰላማዊ ዜጎችን በመግደል ላይ እንደሚገኙ አብዱረህማን ማህዲ የተባሉ በለንደን የኦጋዴን ነፃ አዉጪ ግንባር ተጠሪ ገለፁ። የግንባሩ ተጠሪ ጨምረዉ እንደገለፁት የወያኔ ወታደሮች ሰላማዊ ዜጎች በብዛት ወደ ሚኖሩበት መንደር በመግባት ነዋሪዉን በማሸበር ጭካኔ የተመላበት ተራ ግድያ ሲፈፅሙ ይህ የመጀመሪያ ጊዜ አይደለም ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በቅርቡ ቁጥራቸው በርካታ በሆኑ የደገሃቡር ነዋሪዎች ላይ ግድያ መፈጸሙን የሚቾቹ ዘመዶች ለአሶስየትድ ፕሬስ መግለፃቸዉን ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል። በተመሳሳይ ዜና የወያኔ ተለጣፊ የሆነዉ የሶማሌ ክልል ማስታወቂ ቢሮ ሃላፊ የግንባሩን ክስ መሰረተ ቢስ ፕሮፖጋንዳ ነው በማለት አጣጥሎታል።

የኦጋዴን ነፃ አዉጪ ግንባር በወያኔ ኃይል ተገደሉ ያላቸዉን የ37 ሰዎች ስም ዝርዝር ይፋ ያደረገ ሲሆን ሌሎች ወደ 60 የሚጠጉ የት እንደደረሱ እንደማይታወቅ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ለነፃነታችን የምናደርገው ትግል እና ነፃ ሚዲያ

ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በኣቶዋ ለኢሳት ገንዘብ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ስብሰባ ላይ የቀረበ ኣስተያየት: ኤፕሬል 27 2011 (ክፍል 2 የመጨራሻ ክፍል )

### 7. ዌብ ሳይቶች

ወደ ሃያ የሚጠጉ ለዲሞክራሲ ወገንተኛ የሆኑ ዌብ ሳይቶች አሉ። እነዚህም ዌብ ሳይቶች በጋራ የሚሠሩበት መንገድ ቢፈለግ የተሻለ ውጤት ማምጣት ይቻላል ብዬ እገምታለሁ። የአብዮትን ወቅት እንደ ዘመቻ ጊዜ ማየት አለብን። ስለዚህም እነዚህ በተበታተነ ሁኔታ ያሉት ዌብ ሳይቶች ያላቸውን መረጃ፣ እውቀት፣ ሃብት፣ ኃይል በሙሉ አሰባስበው ኢትዮጵያ ውስጥ የሚደረገውን ትግል ማገዝ በሚችሉበት ሁኔታ መቃኘት ይኖርባቸዋል።

ከዌብ ሳይቶች በተጨማሪም ብሎጎችን በብዛት መጠቀም ይኖርብናል። የመለስ ቅጥረኖች አንዱን ብሎግ ሲያፍኑ አስር አዳዲስ መከፈት ይኖርባቸዋል።

### 8. የአጭር ሞገድ ሬድዮኖች

#### 8.1. በመንግሥታት እጅ ውስጥ ያሉ

የአሜሪካ ድምጽና ዶቸ ቬሌ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ አድማጭ ያላቸው ሬድዮኖች ናቸው። ለአገራችን ህዝብ አማራጭ የዜና ምንጭ በመሆኑ እስካሁን ያበረከቱት አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ቢነሳ ተከታትለው ይዘግባሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፤ እርግጠኛ መሆን ግን አይቻልም።

#### 8.2. በፓርቲዎችና ድርጅቶች እጅ ውስጥ ያሉ

የግንቦት 7 ሬድዮን ጨምሮ ኢትዮጵያዊያን የፓለቲካና ሲቪክ ድርጅቶች የሚመሯቸው አምስት ያህል የአጭር ሞገድ ሬድዮኖች አሉ። የሚያስተላልፉበት ፍሪኬንሲ በብዙ ሰው የማይታወቅ በመሆኑ እነዚህ ሬድዮኖች ብዙዎች የሚገምቱትን ያህል አድማጭ የላቸውም። የእርስ በእርስ የማስተማወቅ ሥራ ቢሰሩ ግን ሁሉም ተጠቃሚዎች ይሆናሉ። በአጠቃላይ አሁን ያሉን የአጭር ሞገድ ሬድዮኖች ኃይላቸውን የሚያቀናጁበት መንገድ ቢፈጠር አሁን ከሚያበረክቱት በላይ የሆነ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችላሉ ብዬ አምናለሁ።

### 9. ቴሌቪዥኖች

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ከሁሉም በላይ ተመራጭ የሆነው ሚዲያ ቴሌቪዥን ነው። የቴሌቪዥን ተመልካች ቁጥር በከፍተኛ መጠን ያደገ ከመሆኑ በላይ ኢትዮጵያዊያን ለኢቲቪ ብለው ቴሌቪዥን መግዛት ካቆሙ ቆይቷል። ስለዚህም ቴሌቪዥን ያለው ሰው - በጣም በከፍተኛ መጠን - የሳተላይት ተጠቃሚ ነው። በአሁኑ ጊዜ ለኢቲቪ ብሎ ገንዘብ የሚያወጣ ሰው የለም።

አልጀዚራ ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ተመልካች አለው። አልጀዚራ የሰሜን አፍሪቃና የመካከለኛው ምስራቅ አብዮትን በመዘገብ እስከዛሬ የሰራው ሥራ በጣም የሚያስመሰግነው ነው። ተመሳሳይ ተግባር ለኢትዮጵያ ያደርጋል ወይ የሚለው ጉዳይ ግን አጠራጣሪ ነው። ከዚህም በተጨማሪ አልጀዚራ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች የሚጠቀም አለመሆኑም ትልቅ ጉዳት ነው።

እስካሁን ድረስ በአገር ልጆች እና በአገራችን ቋንቋ የሚቀርብ ለዲሞክራሲ ወገንተኛ የሆነ ቴሌቪዥን **ኢሳት** ብቻ ነው። በነገራችን ላይ ለኢሳትም ተለጣፊ እንደተሰራለት ታውቃላችሁ ብዬ እገምታለሁ። ኢ. ቢ. ኤስ የሚባል ተለጣፊ የሳተላይት ቴሌቪዥን ተቋቁሟል። ይሁን እንጂ ተመልካቹ በኢቢኤስ እና በኢቲቪ መካከል ልዩነት ስላላየ መኖሩ እንኳ እጅግም አይታወቅም።

ኢትዮጵያ ውስጥ የሚነሳውን ህዝባዊ አብዮትን ተከታትሎ ለመዘገብ ኢሳትን የመሰለ የመረጃ አውታር የለንም። በአጭር ጊዜ ውስጥ አሁን ከሚያስተላልፍበት አማርኛ በተጨማሪ የኦሮምኛ ፕሮግራም ቢችል እና በሌሎችም ቋንቋዎች ዝግጅቱን ለማቅረብ ቢተጋ ጥሩ ነው። ኢሳት ለጊዜው ምትክም ተተኪም የሌለው የቴሌቪዥን ጣብያ ነው።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ የኢሳትን አቅም በመረዳቱ ነው ገና ከንጋቱ በራሱ የሚመራ ኮሚቴ አቋቁሞ የሞገድ ጦርነቱን የከፈተበት። ያም ሆኖ ግን ኢሳት በአጭር ጊዜ ውስጥ "የኢትዮጵያ መብራት" ተባለ። መለስ ኢሳትን በአፈነ ቁጥር "ዓይናችን ጠፋ" "ጨለማ ዋጠን" የሚል እሮሮ ይሰማል። ኢሳት አየር ላይ በመሆን ብቻ ሳይሆን በአየር ላይ ተመትቶ ሲወርድም ህዝብን ያነሳሳል። ኢሳት ለኛ ከቴሌቪዥን እጅግ በላይ ነው። ሲመታም ኢሳት የኛው መሃመድ ቦዛዚ ነው።

ኢሳት ሞገድን ሲቋቋም የሳተላይት ካምፓኒዎችን በማባበል በአየር እንዲወርድ የተደረገበት ጊዜ አለ። ኢሳትን ለማዳን ሰልፍ መውጣት ካስፈለገም መውጣት ይኖርብናል። ኢሳት የኢትዮጵያ ሃብት ነው። ኢሳት የኢትዮጵያ አልጀዚራ ነው። ለነፃነት የምናደርገውን ትግል እዳር ለማድረስ ከሚያስፈልጉን ግብዓቶች ዋነኛው ኢሳት ነው። ኢሳት ከእኛ ገንዘብ ብቻ ሳይሆን የእውቀት፣ የጊዜ፣ የሞራል ድጋፍ ይፈልጋል። ቅድም እንዳልኩት ምናልባት አቤቱታዎችም (petitions) መፃፍ እና ሰልፍ መውጣት ሁሉ ሊጠይቀን ይችላል።

### ህዝባዊ ጋዜጠኝነት

እስካሁን የተናገርኩት ስለመረጃ አውታሮች ነው። "መረጃዎቹስ እንዴት ይገኛሉ?" የሚለው ጥያቄም መሠረታዊ ነው። ለዚህ ያለኝ ምላሽ "ህዝባዊ ጋዜጠኝነትን ማዳበር" የሚል ነው። ህዝባዊ ጋዜጠኝነት በእንግሊዝኛ Citizen journalism, public journalism, participatory journalism, አንዳዴም street journalism እየተባለ የሚጠራው የጋዜጠኝነት ዓይነት ነው። በዚህ የጋዜጠኝነት ጽንሰ ሃሳብ መሰረት ሁሉም ዜጋ ጋዜጠኛ ነው። ማንኛውም ነፃነቱንና አገሩን የሚወድ ዜጋ የጋዜጠኝነት ሙያና ዝንባሌ ኖረውም አልኖረው መረጃዎችና ዜናዎችን በመሰብሰብ፣ በማጠናቀር፣ በመተንተንና በማሰራጨት ሥራዎች ውስጥ በንቃት መሳተፍ ይኖርበታል።

በኃላፊነት ስሜት ከተሰራ ህዝባዊ ጋዜጠኝነት ትክክለኛ የሆኑ መረጃዎችን በፍጥነት ለማግኘት ያስችላል። በተለይም በአሁኑ ሰዓት የድምጽና የምስል መቅረጫዎችን በኪሶቻችን ይዘን የምንዞር በመሆኑ እነዚህን በእጃችን የሚገኙ ቁሳቁሶችን በአግባቡ መጠቀምን መልመድ ይኖርብናል። በኢትዮጵያ የሚገኙ ዜጎች የተለየ ሁኔታ ሲያዩ በተንቀሳቃሽ ስልኮቻቸው አማካይነት የመቅረጽና ወዲያውኑ የመላክ ልምድ እንዲያዳብሩ ማድረግ ይኖርብናል። ለአንዳንድ ንቁ ዘጋቢዎቻችን ደግሞ የተሻሻሉ መሣሪያዎችን ማሟላት ይጠበቅብናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ወገናችንን ሁሉ ጋዜጠኛ ካደረግነው አንዳችም የሚሸሸግ ምስጢር አይኖርም። ከበረታን እስር ቤት የሚፈፀመውን ሰቆቃ ሳይቀር በድብቅ ካሜራዎች እየቀረጽን ለህዝባችን ብቻ ሳይሆን ለሄግ ችሎት ማቅረብ እንችላለን።

አንድ ጉዳይ ላሰምርበት እፈልጋለሁ። **ያልተዘገበ ህዝባዊ አመጽ ጭራሹን እንዳልነበረ ይቆጠራል።** ለምሳሌ በአንድ ከተማ ውስጥ አመጽ ተቀስቅሶ እያለ ምንም ካልተዘገበ፣ አንዳችም ምስል ከሌለ አመጹ የነበረ ስለመሆኑ ማሳመን እንኳን ይከብዳል። በአመጹ የሞቱ፣ የተጎዱ ሁሉ ደማቸው ደመ-ከልብ ይሆናል። መለስ እስከዛሬ ድረስ በህዝባችን ላይ ሰቆቃ የሚያደርሰው ህዝባችንን ጨለማ ውስጥ አጉሮ ነው። የመለስን የጭካኔ እርምጃዎች እየተከታተልን በምስል ማጋለጥ ከቻልን የነፃነታችን ቀን እናቀርባለን። ህዝብ ሲተባበር ትልቁን የመረጃ ወንዝ ይፈጥራል። **ሁላችንም ጋዜጠኞች ከሆንን ከኛ የሚያመልጥ ዜና እንዳይኖር ማድረግ እንችላለን።**

በህዝባዊ ጋዜጠኝነት አድማጮች እና/ወይም ተመልካቾች የሚሰሙት ራሳቸው የተሳተፉበት ዜና እንጂ የአንድ ወገን ሰበካ ወይም ፕሮፖጋንዳ አይደለም። አድማጩም ራሱ ስለታዘበው ነገር የሚሰማ በመሆኑ ዜናው ተዓማኒ ነው።

ህዝባዊ ጋዜጠኝነት የራሱ ድክመቶች የሉትም ማለት አይደለም። ፕሮፌሽናል ጋዜጠኝነት የሚፈለግባቸው በርካታ ጊዜዓት እንዳሉ ምንም ጥርጥር የለውም። በቅርቡ እንገባበታለን ለምለው ህዝባዊ አብዮት ግን ፕሮፌሽናል ጋዜጠኝነት በህዝባዊ ጋዜጠኝነት ካልታገዘ ወቅቱ የሚፈልገውን አገልግሎት መስጠት አይችልም። ስለሆነም ሁላችንም ከዛሬ ጀምሮ ጋዜጠኞች እንሁን። ኢትዮጵያ ለሚገኙ ወገኖቻችንም የተሻሻሉ የሞባይል ቀፎዎችን በመላክ እናሳትፋቸው።

### ድርጅት

በሰሜን አፍሪቃና መካከለኛው ምሥራቅ የታየው ህዝባዊ አብዮት ኢትዮጵያ ውስጥ ሊከሰት አይችልም የሚሉ ሰዎች ዋነኛ መከራከሪያቸው የኢንተርኔት ስርጭት አነስተኛነት፣ የአልጀዚራ አለመኖር፣ የተማረ ህዝብ ማነስ እና የመሳሰለው ነው።

ከዚህ በፊትም እንደጠቀስኩት የኛ መተማመኛችን የወጣቱ የፈጠራ ችሎታ ነው። እኔ በጥሞና ሳስብ ይህን ያህል አማራጭ ካገኙሁ ወጣቶች ምን ያህል ድንቅ ሃሳቦችን እንደሚያፈልቁ ገምቱ!!! በነፃነት ማሰብ የጀመረ ጭንቅላት ለችግሮች መፍትሄ አያጣም። እኔ በወጣቶች የፈጠራ ችሎታ ላይ ከፍተኛ እምነት አለኝ። አቅጣጫውን ካሳየናቸው መሸሎከለኪያዎቹን እነሱ ያገኟቸዋል።

የኛ ትልቁ እርዳታ መሆን ያለበት ተቋማትን መፍጠር ነው። የሚዲያ ባለሙያዎች ተሰባስበው አንድ ተቋም የመፍጠሪያቸው ጊዜ አሁን ነው ብዬ አምናለሁ። ይህ ማዕከል አማራጭ የዜና አውታሮችን ስለመጠቀም ብቻ ሳይሆን የዜና ኢጀንሲና የመረጃ ማዕከሎችን ስለመፍጠር ማሰብ ይኖርበታል።

ሁላችንም እንደምናውቀው ኢትዮጵያ የትላልቅ የዜና ድርጅቶችን ትኩረት የምትስብ አገር አይደለችም። የመለስ አገዛዝ ደግሞ ህዝቡን ከማናቸውም ዜና ከልሎ በሌለ የልማት መዝሙር እያደነቆረው ነው። ለአገራችን መድረስ የምንችለው እኛው ብቻ ነው። መተማመን ያለብን በራሳችን ነው። በራሳችን ኃይል ይህንን ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት መጣል እና በምትኩም ፍትህ የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን መፍጠር ግዴታችን ነው። እኛ ይህን ማድረግ እንችላለን።

### ማጠቃለያ

ክብራትና ክቡራን!

የዛሬ ንግግሬ ከጠበቃችሁት በላይ በዝርዝር ጉዳይ እንደገባሁባችሁ እገምታለሁ። አሁን ያለነው ለታላቅ ህዝባዊ አብዮት ዝግጅት በሚደረግበት ወቅት ውስጥ ነው። የምናደርገው ዝግጅት ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ መግባት ይኖርበታል። ይህ እድል ሊያመልጠን ከቶ አይገባም። ይህን እድል ተጠቅመን ህዝብ በአሸናፊነት እንዲወጣ አስፈላጊውን ሁሉ ዝግጅት ማድረግ ይኖርብናል። በሌሎች አገሮች የነበሩ፤ እኛ ዘንዳ ግን የሌሉ ነገሮችን ማሟላት የኛ ተግባር ነው። ከነዚህም ዋነኛው ሚዲያ ነው።

ንግግሬን በአራት ጭብጦች ብቻ ላጠቃልል

1. ኢሳት ዓይናችን ነው። ኢሳት አልጀዚራችን ነው። ስለሆነም እንንከባከበው፤ እንደግፈው፤
2. ሌሎችም አማራጮችን እንፈልግ።
3. ዓለም ዓቀፍ የሚዲያ ኮሚቴ እናቋቁም።
4. ሁላችንም ጋዜጠኞች እንሁን።

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ እጅግ በሙስና የተጨማለቀ መሆኑ በግልጽ እየታየ ርዳታ ለጋሽ ሃገራት ጆሮ ዳባ ልበስ ማለታቸው አሳፋሪ ነው ተባለ

የብሪቲሽ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን ቢቢሲ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ባለፈው አርብ ግንቦት 21 ቀን ታዋቂ ጋዜጠኞችና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ከፍተኛ የእንግሊዝ መንግስት ባለስልጣናት በተገኙበት የጠረቤዛ ዙሪያ ውይይት ያደረገ ሲሆን በውይይቱ ወቅት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዉስጡና ዉጬ በሙስና የተጨማለቀ አገዛዝ መሆኑ እየታወቀ ብሪታኒያም ሆነች ሌሎች ምዕራባዊያን አገሮች በዚህ ዘረኛና ሙሰኛ አገዛዝ ላይ ለሚቀርቡ አሉታዊ ሪፖርቶች ምንም ጆሮ አለመስጠታቸውና ተገቢ እርምጃ አለመውሰዳቸው እጅግ አሳፋሪ እንደሆነ አንድ የዉይይቱ ተሳታፊ ገለጹ።

በዚህ የእንግሊዝ መንግስት ለታዳጊ አገሮች በሚያደርገው የልማት እርዳታዎች ዙሪያ ባተኮረው ውይይት ኢትዮጵያን በሚመለከት የተናገሩት የዉይይቱ ተሳታፊ እንዲህ ነበር ያሉት።

“እስከዛሬ ድረስ በየትኛውም መድረክ በድፍረት የማይነሳን ሃሳብ ለማንሳት እፈልጋለሁ። ከርዳታ ጋር በተያያዘ የእንግሊዝ መንግስት የሚያደርገውን ሰብዓዊ እርዳታ እኔም የምደግፈው ነውና ችግር የለብኝም ፣ ነገር ግን ከመንግስትም በላይ የእንግሊዝ ሌበር ፓርቲን እጅግ መውቀስ እፈልጋለሁ። የእንግሊዝ መንግስት ለተለያዩ አገሮች የሚሰጣቸውን የልማት እርዳታ የታክስ ከፋዩ የእንግሊዝ ህዝብ ገንዘብ ለታዳጊ አገሮች ስለመሰጠቱ እንጂ እርዳታ ተቀባይ አገሮች የሚሰጣቸዉን ገንዘብ በምን መልኩ እንደሚጠቀሙበት ምንም አይነት እውነተኛ ክትትል አያደርግም።፣ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ስለምዘዋወር በዚህ የልማት ርዳታ ዙሪያ የተወሰነ ግንዛቤ ያለኝ ሰው ነኝ። ስለሆነም ከመንግስታችን በልማት ርዳታ ስም ወደ እርዳታ ተቀባይ አገሮች የሚጎርፈው ገንዘብ አጠቃቀም ምን እንደሚመስል የራሴን ግንዛቤ ወስጃለሁ። ይህ የእርዳታ ገንዘብ በሙስና በተጨማለቁ የፖለቲካ መሪዎች አማካኝነት ተመልሶ ወደ ስዊዝ ባንክ እየመጣ ለመሆኑ ምንም የሚያጠራጥር አይደለም። ለዚህም አንድ ዋነኛ ምሳሌ ልስጣችሁ፣ “የኢትዮጵያ የስብዓዊ መብቶች ጠባቂ” በመባል የሚታወቀው ተቋም፣ የኢትዮጵያ መንግስት የልማት ርዳታን በምን መልኩ እየመዘበረው እንደሆነ በጥናት በተደገፈ መረጃ በግልፅ አጋልጧል። በኢትዮጵያ ያለው አገዛዝ ማአይስት የሆነ ሶሻሊስት አገዛዝ ነው። የኢትዮጵያ መንስግስት ብሪታኒያ ለታዳጊ አገሮች በየአመቱ ከምትሰጠዉ እርዳታ ከፍተኛዉን ድርሻ የሚወስድ መንግስት ነዉ፤ ብሪታኒያም ሆነች ሌሎች ለጋሽ አገሮች ገንዘቡን በቀጥታ ለአገዛዙ ይሰጣሉ፣ አገዛዙ ደግሞ ፍጹም በሙስና የተጨማለቀ አገዛዝ ነው፣ ፣ ይህ መሆኑ እየታወቀ እንግሊዝም ሆነች ሌሎች አገሮች ተፈጸመ የተባለውን ምዝበራ ለማጣራት ትንሽም ቢሆን ሙከራ አለማድረጋቸው ወይንም ፍላጎት አለማሳየታቸው፣ በጣም አሳፋሪና አሳዛኝ ድርጊት ነው፣ ፣ ሂዩማን ራይትስ ዋች በግልጽ እንዳስቀመጠው እንዲህ አይነቱ አካሄድ እጅግ አደገኛ እንደሆነ በአንክሮ ገልጿል። ሂዩማን ሪይትስ ዋች ባቀረበው ሪፖርት ዙሪያ የኢትዮጵያው አገዛዝ ከፍተኛ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ ከበርካታ ወራት በፊት ጀምሮ በማድረግ ላይ ይገኛል። ሀሳቤን ለማጠቃለል የእንግሊዝ መንግስትም ሆነ ሌሎች ምዕራባዊያን አገሮች እንዲህ ላለው ወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል በማለት ሃሳባቸውን አጠቃልለዋል።

አስተያየት ሰጪው ሃሳባቸውን ሲያጠቃልሉ የዉይይቱ ተሳታፊዎች በከፍተኛ ጭብጨባ ሀሳቡ ተቀባይነት ያለው መሆኑን የገለጸ ሲሆን፣ የእንግሊዝ መንግስት ባለስልጣናት እራሳቸውን ለመከላከል ሙከራ ሲያደርጉ ተስተዉለዋል።

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ የልማት ርዳታን ለፖለቲካዊ ፍጆታ እያዋለ ነው በማለት ሂዩማን ራይትስ ዋች በጥናት ላይ የተመሰረተ ሪፖርት ከበርካታ ወራት በፊት ማቅረቡ አይዘነጋም።

## የህዝቦች የዲሞክራሲ መብት መጠበቅ የአሜሪካ ቀዳሚ አጀንዳ እንደሆነ ፕሬዝዳንት ኦባማ አስታወቁ

በአረቡ አለም ህዝባዊ የለዉጥ እንቅስቃሴ ከተቀሰቀሰ ወዲህ ባለፈዉ ሃሙስ ለመጀመሪያ የመካከለኛዉ ምስራቅንና የሰሜን አፍሪቃ አገሮችን አስመልክተዉ ለአገራቸውና ለመላው አለም ህዝብ ንግግር ያደረጉት የአሜሪካዉ ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ አሜሪካ አገሮች ወደ ዲሞክራሲ የሚደርጉትን ሽግግር እንደምትደግፍ ገለፁ።

በቅርቡ በተባበረ ህዝባዊ አመጽ አምባገነኖችን ከስልጣን አባርረዉ ዲሞክራሲያዊ ሽግግር በማድረግ ላይ ለሚገኙት ለግብፅና ቱኒዝያ ግዜያዊ አስተዳደሮች አገራቸዉ አሜሪካ ተጨማሪ እርዳታ እንደምታደርግ የገለፁት ፕሬዚዳንት ኦባማ፤ የሶሪያን ህዝብ የለዉጥና የመብት ጥያቄ በሃይል ለመጨፍለቅ ዜጎቻቸዉን በመግደል ላይ የሚገኙት የሶሪያዉ ፕሬዝዳንት በሺር አል አሳድ ዲሞክራሲን መቀበል ያለበለዚያ ገለል ማለት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ፕሬዝዳንቱ በዚሁ ንግግራቸዉ ዲሞክራሲ እንዲያድግና እንዲበለፅግ አገሮቹ ኢኮኖሚያቸዉን ማሻሻልና ለወጣቱ ትዉልድ የስራ እድል መፍጠር እንደሚገባቸዉ አሳስበዋል። የክልሉ መረጋጋት የመንግስታቸዉ የፖለቲካ ፍላጎት መሆኑን የገልጹት ፕሬዚዳንት ኦባማ አስተዳደራቸዉ በክልሉ ውስጥ የህዝብ ድምጽ ተሰሚነት እንዲኖረውና በመንግሥትና በህዝብ መካከል የተፈጠረው ክፍተት ወደ ዲሞክራሲ በሚደረግ ሽግግር እልባት እንዲያገኝ አስፈላጊዉን ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል።

ከዚህ በተጨማሪ መንግስታቸዉ ግብፅ ለዜጎቿ የስራ እድል ለመፍጠር እንዲረዳት የአንድ ቢሊዮን ዶላር የብድር ስረዛ እንደሚያደርግና የለዉጥ ምሳሌ የሆኑት ግብፅና ቱኒዚያ ብድር፡ የንግድና ሌሎች አለም አቀፍ ድጋፎች የሚያገኙበት መንገድ ሊኖር እንደሚችል ፕሬዚዳንቱ አብራርተዋል።

ፕሬዝዳንት ኦባማ ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት የአገራቸዉ ኤኮኖሚ በአስተማማኝ ደረጃ ላይ ባይገኝም አገሮቹን በገንዘብና በሃሳብ የመደገፍ ግዴታ እንዳለባት ለአሜሪካን ህዝብ ከማሳሰባቸዉም በላይ አገራቸዉ ለሰብአዊ መብት መከበር ከሚቆሙ ሃይሎች ጎን እንደምትሰለፍ ለአለም አቀፉ ህብረተሰብ አረጋግጠዋል።

የፕሬዝዳንት ኦባማ ንግግር በሶስት አቢይ ነጥቦች ዙሪያ የተከፈለ ሲሆን፡ በመካከለኛዉ ምስራቅና በሰሜን አሜሪካ ያለዉ የለዉጥ እንቅስቃሴ ግምገማ፤ አገራቸዉ የምትሰጠዉ ኢኮኖሚያዊ እርዳታ እና እስራኤልና ፍልስጤምን ጨምሮ የአካባቢዉን ሰላምና ፀጥታ አካትቶአል።

ለዘመናት የቆየውን የእስራኤልንና የፍልስጤምን ችግር አስመልክቶ ሁለቱም ወገኖች እኤአ በ1967 በነበራቸዉ ይዞታዎች ላይ ተመርኩዞው ውዝግባቸውን በድርድር መፈታት እንዳለባቸውና ህልውናዋ በተጠበቀ እስራኤል አጠገብ ፍልስጤማዉያን የራሳቸውን ነጻ አገር መስርተው መኖር እንደሚችሉ አስተዳደራቸዉ እንደሚያምን ገልፀዉ ሁለቱም ወገኖች ተቀራርበዉ ዉዝግባቸዉን እስካልፈቱ ድረስ ይበልጥ ሊጎዱ እንደሚችሉ አስጠንቅቀዋል።

አሜሪካ የሶሪያ መንግስት በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ በመዉሰድ ላይ ባለዉ ግድያ እስራትና ድብደባ ምክንያት የፕሬዝዳንት በሺር አል አሳድና የሌሎች ስድስት ባለስልጣኖቻቸዉ ገንዘብና ንብረት እንዳይንቀሳቀስ ማገዷ ይታወሳል። ሆኖም ይህ በእንዲህ እንዳለ በባህሬን፤ በየመንና ፤ በሶሪያ በተነሳው ህዝባዊ አመጽ በጭካኔ እየተጨፈጨፉ ላሉት ህዝቦች የምዕራቡ አለም በቂ ትኩረት አልሰጠም የሚል ትችት በብዛት በመሰንዘር ላይ መሆኑ ተዉቋል።

### ሃያ የክህደት፣ የውርደት፣ የዘረኛነትና የዘራፊነት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

2. ያለፉት 20 አመታት ሃገሪቱ በጥቂት ለዘረፋ ስልጣን በያዙ ዘረኞችና አፋኞች እጅ በመወደቋ ታላቅ የተፈጥሮና የሰው ሃብቷንና እንዲሁም ባለፈው 20 አመታት የተገኘው አንጻራዊ ሰላም ተጠቅም ድህነትን ረሃብን ስደትን ሀገራዊ ውርደትን ማስቆም የምትችልበትን እጅግ ታላቅ እድል ያባከነችባቸው አመታት ናቸው።
3. ያለፉት 20 አመታት፣ በየትኛዎቹም ኢትዮጵያ መንግስታዊ ስርአቶች ከቶ ተደርገው የማይታወቁ፤ በሃገራችንና በህዝቧ ብሄራዊ ጥቅምና ደህንነት ላይ ከፍተኛ ሃገራዊ ክህደቶች የተፈጸሙባቸው አመታት ናቸው። ኢትዮጵያችን ከዚህች ሃገር ውስጥ በወጡ ልጆቿ ሳይሆን ለሃገሪቱና ለህዝቧ ከፍተኛ ጥላቻ ባላቸው፤ ሃገሪቱንና ህዝቧን መበቀል የግድ የሆነባቸው፤ ቂም አዝለው ስልጣን በያዙ የውጭ ወራሪዎች እጅ የወደቀች እስክትመስል ሃገራዊና ህዝባዊ ክብሯ አጥታ የተዋረደችባቸው አመታት ናቸው።
4. ያለፉት 20 አመታት በየትኛውም ዘመን ስልጣን ላይ የወጡ ገዥዎች አስበውትና አድርገውት በማያውቁት ደረጃ የሃገር ሃብትና ቅርስ ስልጣን ላይ ባሉ ጥቂት የትግራይ ገዥ ጉጅሌ አባላት እየተዘረፈ በባእድ ሃገራት የተከማቸበት አመታት ናቸው። እኝህ አመታት የዘረኛው ገዥ ጉጅሌ አባላት ለዘረፋ እንዲያመቻቸው ያስጠጓቸው የውጭ ሃገራት ዜጎች በሃገራችን ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ የህዝቡን ለም መሬት፣ ወርቅ ሌላም ማእድን እንዳሻቸው እየዘረፉና የሃገሪቱን ህዝብ ከባርነት ስርአት ባለተናነሰ የጌታና የሎሌ ግንኙነት እንዳሻቸው እያዋረዱ እንዲያሰሩ ስድ የተለቀቁባቸው አመታት ናቸው።
5. ያለፉት 20 አመታት ዳኝነትና ፍትህ የሚባል ነገር ጭራሽኑ ካገር የጠፋበት፤ ዜጎችና ህዝቦች ተቆጪ በሌላቸው በዘርና በጥቅም በተሳሰሩ የገዢው ጉጅሌ የጦር አዛዦች፣ የደህንነት አባላትና ካድሬዎች እንዳሻቸው የሚረሸኑበት፤ ህዝብ ለሰቆቃና ለእስራት የተዳረገበት፤ ሰው በገዛ ቤቱ ውስጥ ሳይቀር የሚሰማውን መናገር እንዳይችል የስጋትና የፍርሃት ቀንበር ውስጥ የወደቀችባቸው፤ እንዲሁም በዘር ማጥፋትና በሰው ልጆች ላይ እንደተፈጸሙ ተደርገው የሚታዩና በአለምአቀፋዊ ወንጀለኛነት የሚያስጠይቁ ታላላቅ ወንጀሎች በመላው ሃገሪቱ ህዝብ ላይ የተፈጸሙባቸው አመታት ናቸው።

በጥቅሉ ያለፉት 20 የወያኔ የግዛት አመታት የኢትዮጵያን ውርደት፤ የህዝቧን የድህነት፣ የባርነትና የሰቆቃ ህይወት በማየት በሚደሰቱ ጸረ ሃገርና ህዝብ ሃይሎች እጅ ወድቃ አበሳዋን ያየችባቸው አመታት ናቸው። ግንቦት 20 የተባለውን የዛሬውን የወያኔዎች በአል የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያስበው፣ በሃዘን በቁጭትና በንዴት ነው። የወያኔ እድሜ እንዲረዝም ሳይሆን እንዲያጥር በመመኘት፣ በመጸለይ፣ በመደራጀትና በመታገል ነው። የግንቦት7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ስሜትም ከህዝብ ስሜት የተለያ አይደለም። ለዚህም ነው በወያኔ የፈንጠዝያ እለት ውደቀታቸው የማይቀር መሆኑን የምናረዳቸው።

ውድመት ለዘረኛውና ለዘራፊው ጸረ-ሃገርና ጸረ -ህዝብ ጉጅሌ እርገት ለኢትዮጵያ ህዝብ የነጻነት የእኩልነት የፍትህና የአንድነት ፍላጎት

### የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ተራ ግድያ በመፈፀም ላይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ገልጿል።

በክልሉ የሚኖር አንድ ወንድሙ የተገደለበት ሰዉ ለአሶስየትድ ፕሬስ የዜና ወኪል በመደወል እንደተናገረዉ የወያኔ አገዛዝ ከምድር ላይ ሊያጠፉቸዉ እቅድ እንዳለዉና አሁንም ቀንና ማታ ሲለሚከታተለዉ ወደ ኬንያ የመጥፋት ዕቅድ እንዳለዉ መናገሩን ለማወቅ ተችሏል።

ይህ ግንባሩ የሰጠዉ መግለጫ በሌላ ገለልተኛ አካል ያልተረጋገጠ ቢሆንም አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች የወያኔ መንግስት ወታደሮች በነጋ በጠባ በኦጋዴን ክልል ነዋሪዎች ላይ ዘግናኝ የሆኑ የሰቆቃ ወንጀሎችን እንደሚፈጽሙ በተደጋጋሚ ተገልጿል።የአሜሪካ መንግስት የዉጭ ጉዳይ ሚ/ር ባወጣዉ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት የ2010 ሪፖርት ላይ የመንግስት የፀጥታ ሃይሎች በሶማሊያ ክልል ዉስጥ ሰላማዊ ዜጎችን ለመግደላቸዉና የተለያዩየሰብአዊ መብት ጥሰቶች ለመፈፀማቸዉ የታመኑ መረጃዎች መኖራቸዉን ጠቅሷል። ሪፖርቱ በተጨማሪ የሶማሌ ክልል መንግስት ልዩ ፖሊስና የአካባቢ ሚሊሽያ የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃ አዉጪ ደጋፊ ናቸዉ ያሏቸዉን ሰዎች ከመንደራቸዉ አፈናቅለዉ ወደ ሌላ ቦታ እንደወሰዷቸዉ ማስረጃ እንዳለዉ ጠቁሟል።

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ገለልተኛ የሆኑ አካላት ወደ ክልሉ እንዲገቡ እስካልፈቀደ ድረስ በኦጋዴን ዉስጥ የሚደረገዉን ነገር ምንም ማወቅ እንደማይቻል ከዚህ በፊት የሂዩማን ራይትስ ዎች የአፍሪቃ ቀንድ ተመራማሪ ቤን ራዉለንስ መግለፃቸዉ ይታወሳል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የአለም የምግብ ፕሮግራም በቅርቡ በሰራተኞቹ ላይ በደረሰዉ የሞትና የመቁሰል አደጋና እንዲሁም ሁለት ሰራተኞቹ የት እንደደረሱ ባለመታወቁ በሶማሊያ ባለዉ የፀጥታ ችግር ምክንያት በክልሉ የሚያደርገዉን የእርዳታ እንቅስቃሴ እንደሚያቋርጥ አስታዉቋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**
**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**
ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org